# ሃጎስን ፤ በሌንጬ

አብሮህ የታገለው ፤ አምናና ካቻምና
እምነቱ እንዳልነበር ፤ ላብሮነት ዝምድና
ገና ከጅምሩ ፤ ወንበሩም ሳይጠና
ስግብግብ ተፈጥሮው ፤ ሁሉ አማረውና
የቆመለት አቋም ፤ ፈጥኖ ተረሳና
ይዞ የመጣልህ ፤ ገጀራና አጣና
ለጭፈራ አይደለም ፤ ካንተ ጋር ፤ ሊዝናና
ደምህን ፤ ደመ ከልብ ፤ ሊያደርገው ነውና
ቃኘው አካሄድክን ፤ አስብ እንደገና ።

በመጣ ዘውገኛ ፤ ዘወትር መደፍጠጥ
ዛሬም ተመልሰን ፤ ከዕሳት ፤ ወደ ረመጥ
ዓላማ አያሳካም ፤ አዝኖ ፤ ከንፈር መምጠጥ
ወገን ተሰባሰብ ፤ ይብቃህ መለማመጥ
ምክንያት አታብዛ ፤ እስኪ ተደማመጥ
ትግላችን ይፋፋም ፤ ያስጠቃል መቀመጥ
የኬኛው አያያዝ ፤ ጥልቅ ይዞህ ፤ እንዳይሰምጥ ።

የዘውጌ ማንነት ፤ ጭምብል ካጠለቀው
ያየው ፤ ሁሉ የኔ ፤ ብሎ ከሚያስቀው
የነፍሰጡር ጎጆ ፤ ከሚነቀንቀው
የጠገበ ይሻላል ፤ ቁንጣን ያስጨነቀው ፤
ከነ ፤ ሁሉ አማረሽ ፤ አይቶ ከማያውቀው
ጊዜው ፤ የኔ ብሎ ፤ ካለልክ የሞቀው
ህግ ከማይገዛው ፤ ከተሞላቀቀው
ደሃ እያሳደደ ፤ ደሃን ከሚሰርቀው
ቀምቶ የሚበላ ፤ ገጀራ የታጠቀው
አጃኢብ አሰኘን፤ ወያኔን አስናቀው ።

ለውጥማ ፤ ለውጥ አለ ፤ አየን ፤ በነ አብዲሳ
ጎሳውን ሲያሰፍር ፤ አንተን እያስነሳ
ቅሬታን ያስነሳው ፤ የበዛው ወቀሳ
ህዝብ የታገለለት ፤ ዓላማው ሲረሳ
ከሳሹም ዳኛውም ፤ ሲሆኑ ፤ እነ ቱምሳ
የተራበው ጠግቦ ፤ ተብቶ ሲያገሳ
ሲተካ ፤ ብናይ ነው ፤ ሃጎስ ፤ በመገርሳ
ስልቻን ቀንቀሎ ፤ ሸፋፉን ፤ በአንካሳ ።

ወይ ኑሮ ፤ ወይ ኑሮ ፤ ቁርንጬ ፤ ቁርጬ
ለኛው ፤ ስቃይ መግዣ ፤ ጠየቁን መዋጬ
እያደሩ ማነስ ፤ መሆን ፤ ባለ ቁንጬ
አጉል ቦታ ፤ ቆመ ፤ ትግሉ ተንገራግጬ
ዛፍ ፤ ጠፋና ባገር ፤ ለአድባር ፤ እምቧጬ
መተካካ ጀመርን ፤ ሃጎስን ፤ በሌንጬ ።

ታዛቢው

April 5, 2019